IBO IB DIPLOMA PROGRAMME
PROGRAMME DU DIPLÔME DU BI
PROGRAMA DEL DIPLOMA DEL BI

M05/1/A1AMH/SP2/AMH/TZ0/XX

22050016

**AMHARIC A1 – STANDARD LEVEL – PAPER 2**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 2**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL MEDIO – PRUEBA 2**

Friday 6 May 2005 (morning)
Vendredi 6 mai 2005 (matin)
Viernes 6 de mayo de 2005 (mañana)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the Part 3 works you have studied. You may include in your answer a discussion of a Part 2 work of the same genre if relevant. Answers which are not based on a discussion of at least two Part 3 works will not score high marks.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Traitez un seul sujet de composition. Vous devez baser votre réponse sur au moins deux des œuvres de la 3e partie que vous avez étudiées. Le cas échéant, vous pouvez inclure dans votre réponse une discussion sur une œuvre du même genre littéraire étudiée dans la 2e partie du programme. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la 3e partie n'obtiendront pas une note élevée.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Elija un tema de redacción. Su respuesta deberá basarse en al menos dos de las obras estudiadas en la Parte 3. Se podrán hacer comentarios sobre una obra de la Parte 2 del mismo género, si fuera necesario. Las respuestas que no incluyan una discusión sobre al menos dos obras de la Parte 3 no recibirán notas altas.

*ከሚከተሉት በአንዱ ላይ ሀተታ ፃፍ(ፃፊ):: መልስህ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ መመስረት አለበት:: በክፍል ሁለት ስር ከሚገኝ አንድ ተመሳሳይ የስነጽሁፍ ዘርፍ ማጣቀሻ ማስገባት ይፈቀዳል:: በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ ያልተመሰረተ መልስ ከፍተኛ ነጥብ አያስገኝም::*

**ድራማ**

1. ተከታዩን

(ሀ) ድራማን በሚመለከት መጠየቅ ያለበት ዋናው ጥያቄ ስራው አስደሳችና የተለየ ገጠመኝ የሚያቀርብ ነው ወይ የሚለው ነው:: ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ሁለት ድራማዎች በማወዳደር ግለጽ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) ትራጀዲና ኮመዲን የሚለያያቸው ዋናው ነጥብ የሰውን ልጅ የሚያቀርቡበት መንገድ ነው:: አንዱ በሰው ልጅ ታላቅነት ላይ ሲያተኩር ሌላው ድክመቱን ይመለከታል:: ያነበብካቸውን ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ሃሳቡን አስረዳ::

**ረጅም ልቦለድ**

2. ተከታዩን

(ሀ) ግጭት ልቦለድን በፍጥነት ለመረዳት የሚያስችለው ወደዋናው የታሪኩ ጉዳይ አንባቢውን ስለሚመራ ነው:: ይህንን ሃሳብ ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማነፃፀር ግለጽ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) ማንኛውም ልቦለድ ድርጊትና ገፀባህሪያት ሊኖሩት ይገባል:: ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች መሰረት በማድረግ ድርጊትና ገፀባህሪያት የሚቀርቡበትን ሁኔታና ያላቸውን አስተዋጽኦ አስረዳ::

**ስነግጥም**

3. ተከታዩን

(ሀ) ብዙ ግጥሞች በዘይቤ አማካኝነት ንጽጽርን በመጠቀም ግልጽ ያልሆነውን ጉዳይ ግልጽ ያደርጋሉ፡፡ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ሶስት ግጥሞች በመመርኮዝ ግለጽ፡፡

ወይም ቀጣዩን ምረጥ፡፡

(ለ) ግጥሞች የሚወደዱት ስሜታችንን በመንከታቸውና በማራኪነታቸው ነው፡፡ ስራቸውን ያጠናሃቸው ገጣምያን በምን ያህል ደረጃና በምን ዘዴ ማራኪና ስሜትህን የነኩ ስራዎች ለማቅረብ ቻሉ? መልስህ ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች የሚያወዳድር ይሁን፡፡

**ስድንባብ**

4. ተከታዩን

(ሀ) የአንድ ስድ ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) ፀሃፊ በገለፃና በምልልስ አማካኝነት ታሪኩን ይገልፃል፡፡ ስራቸውን ያጠናሃቸው ሁለት ፀሀፍያን ገለፃና ምልልስን እንዴትና ለምን እንደተጠቀሙባቸው አስረዳ፡፡

ወይም ቀጣዩን ምረጥ፡፡

(ለ) የአንድ ስድ ጽሁፍ (ለምሳሌም ተራኪ ወግ) እጅግ ጠቃሚ ክፍሎች የመጀመሪያውና የመጨረሻው አንቀጽዎች ናቸው፡፡ ያነበብካቸውን ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ሃሳቡን አስረዳ፡፡

**አጭር ልቦለድ**

5. ተከታዩን

(ሀ) ያጠናሃቸው ስራዎች ሁለት ደራስያን ገፀባህርያቶቻቸውን እንዴት እንደፈጠርዋቸውና እንዳቀረብዋቸው አወዳድር፡፡ አቀራረባቸው ገፀባህርያቱ በልቦለዱ ውስጥ ያላቸውን ሚና በማጉላት ረገድ ያደረጉትን አስተዋጽኦ አስረዳ፡፡

ወይም ቀጣዩን ምረጥ፡፡

(ለ) ባጠናሃቸው ሁለት አጭር ልቦለዶች ውስጥ ጡዘት (ክላይማክስ) እንዴት እንደቀረበና ለእንዳንዱ ስራ ያበረከተው አስተዋጽኦ ምን እንደሆነ ግለጽ፡፡

**ሁለገብ (አጠቃላይ)**

6. ከሚከተሉት አንዱን መርጠህ መልስ(ሽ)::

(ሀ) ስነጽሁፍ ስለገጠመኞች የሚነግረን ሳይሆን በምናባችን (ኤማጅኔሽን) ተሳታፊ እንድንሆን የሚያደርግ ነው:: ይህንን ሃሳብ ባጠናሃቸው ስራዎች ምሳሌነት አብራራ::

ወይም

(ለ) ስነጽሁፍ እራሳችንንና ሌሎችንም ሰዎች እንድንረዳ ያደርገናል:: ያጠናሃቸውን ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር ስራዎቹ እራስህንና ሌሎችን እንድትረዳ ያደረጉትን አስተዋጽኦ አብራራ::

ወይም

(ሐ) ስነጽሁፍ መሰረቱን የጣለው የሰው ልጆች በተፈጥሮ ባላቸው የመደሰት ፍላጎት ላይ ነው:: ደስታ የሚለውን ቃል ምንነት ከገለጽህ በሁዋላ ያነበብካቸው ስራዎች ይህንን የደስታ ስሜት እንደፈጠሩብህ አስረዳ::

ወይም

(መ) በስነጽሁፍ ቃላት በአግባቡና ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ይውላሉ:: ይህንን ሃሳብ ባጠናሃቸው ስራዎች ምሳሌነት አብራራ::